ዜና መጽሔት

ጥር /2016

# ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
# TOURISM TRAINING INSTITUTE

## የዓለም ቱሪዝም ቀን በስልጤ ዞን ወራቤ ተከብሯል፡፡



ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከስልጤ ዞን አስተዳደር ፣ ከወራቤ ዩንቨርስቲ እና ከስልጤ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ቱሪዝም ለአረንጓዴ ልማት፤ አረንጓዴ ልማት ለቱሪዝም በሚል መሪ ቃል በሀገራችን ለ36ኛ ጊዜ የተከበረውን የዓለም ቱሪዝም ቀን በማስመልከት በዞኑ ያዘጋጀው በዓል በሁለት ቀን በጉብኝትና በሌሎች ዝግጅቶች አክብሯል፡፡

በመክፈቻ ፕሮግራሙ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ዴኤታ ዶ/ር ተሻለ በሬቻ እንደገለጹት የዓለም የቱሪዝም ቀን በሀገራችን ለ36ኛ ጊዜ "ቱሪዝም ለአረንጓዴ ልማት፤ አረንጓዴ ልማት ለቱሪዝም" በሚከበረው በዓል ያለንን ዕምቅ የቱሪዝም ሀብቶች መጠቀም የሚያስችል የጥናትና ምርምር ሥራ መሥራትና ሀገርን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚገባ ኢንስቲትዩቱ በዚህ ዘርፍ ከስልጤ ዞን ጋር በመተባበር ማዘጋጀቱን አመስግነዋል።



የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ በበኩላቸው ቱሪዝም የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ግኑኝነትን ማጠናከር የሚችል ዘርፍ በመሆኑ አሁን በስልጤ ዞን የተሰራው ሥራ ወደ ሌሎች ክልሎችና ዞኖች ማስፋትና ማዳረስ መቻል አለብን ብለዋል።

ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ የዞኑን የቱሪዝም ሃብቶች እና መዳረሻዎችን እንዲሁም 18 የሚሆኑ ባህላዊ ምግቦች በሜኑ መልክ አዘጋጅቶ ማቅረብ የሚያስችል ጥናትም በባለሙያዎቹ አስጠንቶ ለዞኑ አስረክቧል።



የመጀመሪያው ቀን የዓለም ቱሪዝም ቀንን አስመልክቶ በቀረበ የጥናታዊ ጽሁፍ መነሻ በተካሄደ የውይይት መድረክ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አቶ ንጉሱ ጥላሁን እንዳሉት ኢትዮጵያ መልከ ብዙ ናት ገና ያልተዳሰሱ ፣ ያልታዩ ብዙ ሃብቶች አሉን እነሱን ማልማት፣ ማስተዋወቅ ይገባናል።

የቱሪዝም ሃብቶች ሸፍነን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ በቁጭት እያነሳን መሄድ የለብንም ብለዋል።

ሌሎች የሥራ ኃላፊዎችና የዞኑ ነዋሪዎች ፣ የማዕከላዊ ደቡብ ኢትዮጵያ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ በቀረቡ ሰነዶች ዙሪያ ሃሳብ ተሰጥተዋል ። በስልጤ ዞን ላይ ያየነው የቱሪዝም ሃብት ዳብሮ ለምቶ የክልሉን ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ትልቅ መዳረሻ እንዲሆን የሚመለከተው ሁሉም መሳተፍ ይጠበቅበታል ብለዋል።







የፓናል ውይይት መነሻ የሆኑ ከመሪ ቃሉ ጋር የተያያዘ የኢንስቲትዩቱ አሰልጣኝ አለምነህ መርሻ ፣ የወራቤ ዩንቨርሲቲ መምህር አንዋር አያኖ ስለ ወራቤ የቱሪስት መስህብ ስፍራዎች እና ስለ ሃላል ቱሪዝም በአሰልጣኝ ሰይድ የሱፍ ቀርቧል።



የሁለተኛውን ቀን ፕሮግራም የከፈቱት በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አቶ ንጉሱ ጥላሁን እንዳሉት ቱሪዝም በአሁኑ ጊዜ ለዜጎች ሥራ እድል በመፍጠር የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ዘርፍ መሆኑን በመጠቆም የስልጤ ዞን ከቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በጥናት የተደገፈ የቱሪስት ማፕ መዘጋጀቱ በባለሙያዎች ሲነሳ የነበረውን አንድ ችግር የሚፈታ መሆኑ ለዞኑ ትልቅ ውጤት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የስልጤ ዞን አስተዳዳሪ አቶ ዓሊ ከድር በበኩላቸው ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በዞኑ የቱሪስት መስህብ የሆኑ ቦታዎች ቢኖሩም አስካሁን ድረስ በባለሙያ ያልተጠኑ እና በቂ መረጃ የሌላቸው እንኳን ከዞኑ ውጪ ያለው ሰው የዞኑ ነዋሪዎችም በበቂ ትውውቅ ያልተደረገበት እንደሆነ ጠቁመው ኢንስቲትዩቱ ለሰራው ሥራ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

በኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

በዞኑ አቋርጠው የሚያልፉ ተጓዦች በቦታው ቆይታ ማድረግ የሚያስችሉ፣ በአጭር ጉዞ ከአዲስ አበባ ተነስተው ለሚመጡ እንዲሁም በዞኑ ሁለት ሶስት ቀን ቆይታ በማድርገ መጎብኘት የሚችሉ ሥፍራዎች መኖራቸውን በኢንስቲትዩቱ የቱሪዝም መምህርና የአጥኚ ቡድኑ አባል አቶ በቀለ ኡማ ገለፃ ተደርጓል፡፡
የምግብ ዝግጅት ቡድኑ አባልና የኢንስቲትዩቱ ምግብና መጠጥ ትምህርት ክፍል አስተባባሪ አቶ ጌታሁን ደሳለኝም የዞኑን ባህላዊ ምግብ በሆቴሎችና በሬስቶራንቶች በሜኑ መልክ ቀርበው ሊሰሩ የሚችሉበት ደረጃ ከዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጋር ሰርተው 18 ዓይነት ምግቦችን አቅርበዋል፡፡
በተጨማሪም አንድ የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራ ሀር አሽ እጣን"በስልጢኛ እጣን አጪሸበት የሚል ትርጉም ያለውን ሀይቅ በእንግዶች ተጎብኝቷል።
ሀይቁ ባለውብ ቀለም እና በዛፎች የተከበበው ነው። ይህ ሀይቅ ለጎብኚዎች ክፍት እንዲሆን የልማት ሥራዎች የሚፈልግ በመሆኑ ዞኑ በትኩረት ሊሠራበት እንደሚገባ በቦታው የተገኙ ጎብኚዎች ተናግረዋል።
ዝግጅቱ የብሔረሰቡ ባህላዊ ምግብ አተካኖ እና ኢንስቲትዩቱ ባዘጋጀው ዕለቱንና ቦታውን የሚወክል ኬክ ቆረሳ እና በሀገር ሽማግሌዎች ምረቃ ፕሮግራሙ ተጠናቋል።





2

## ወራዊ የቱሪዝም መሪዎች ወግ በተለያዩ ዕርሶች






ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሀገር በቀል እውቀት ለቱሪዝም በሚል መሪ ቃል ለሶስት ጊዜ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሄደ፡፡

በዚህ የውይይት መድረከ የተገኙት የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ እንድገለጹት ለአንድ ሀገር መበልጸግ የሀገር በቀል እውቀትን በጥናትና ምርምር በማስደገፍ መሥራት ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ሆኗል፤ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ብዛት ያለው የሰው ኃይል የሚፈልግ እና ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ በመሆኑ ለዘርፉ እድገት የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ አስፈላጊ እንደሆነ ተናግርዋል፡፡
"ሀገር በቀል" ዕውቀት ያላለማነውና ያልተጠቀምነው ሀብት በሚል ርዕስ የውይይት መነሻ ጽሑፍ ያቀረቡት የኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ የምርምር ባለሙያ ዶ/ር ታግሎ ካሳ ናቸው ፡፡
ኢትዮጵያ ምን አላት? ኪነ ህንጻ ፣የመድሃኒት ቅመማና ህክምና፣ስርዓተ ትምህርት ስነ ስዕል፣ ስነ ጠፈር ስነ ጹሁፍ ፣ግብርና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣የግጭትአፈታት ዜዴዎች እና የመሳሰሉት ለቱሪዝም ምቹ ማደርግ እንዴት እንደሚቻል ጭምር የሚገልጽ ጽሁፍ አቅርበዋል፡፡
ይህን ሀገር በቀል ዕውቀት እንዴት በተሻለ እንጠቀም? የትኛውን ብንጠቅም አዋጭ የቱሪስት መስህብ ይሆናል? ሽግግሩ እንዳይቋረጥ ምን መደርግ አለበት የሚሉ ሀሳቦቸ ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡
ከተሳታፊዎቸ መካከል ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም እንድገለጹት የኢትጵያ ቱሪዝም ሀብት የሚታይ ብቻ ሳይሆን በልምድ እና አብሮ በመዋል በማደር የሚጎበኝ እየሆነ መጥቷል ስለሆነም ይህ ደግሞ እኛ ልንሰራበትና ያለንን ሀገራዊ ሀብት ለመጠቀም ግድ ይለናል ብሏል፡፡

ከገጽ 2 የቀጠለ

ውይይቱን የመሩት የኢንስቲትዩቱ አሰልጣኝ ዶ/ር ሳሙኤል መኮንን ከዚህ ውይይት በመነሳት ተቋሙ የተለያዩ የጥናትና ምርምር ስራዎች ሰርቶ የሥልጠናው አካል ሊያደርገው እንደሚችል ተናግረዋል፡፡
ለሁለተኛ ጊዜ ቱሪዝምና የሚዲያ ሚና በሚል ርዕስ ወርሃዊው የቱሪዝም መሪዎች ወግ በቱሪዝም ሙያ ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ጋዜጠኞች እና ሌሎች ተሳታፊዎች በተገኙበት አካሂዷል፡፡







የውይይት መድረኩን አስመልክቶ የኢንስቲትዩቱ ጥናትና ምርምር ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ስዩም እንደተናገሩት በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች፣ ባለሃብቶችና የመንግስት አካላት በየወሩ በተመረጡ ርዕሶች ዙሪያ እየተገናኙ ዘርፉ ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን እንዲለዩ ፣በጋራ መፍትሔ እንዲያመጡ ታስቦ እየተሰራ መሆኑን ገልጸው ከዚህ ቀደም በነበሩት መድረኮች የተገኙ



ግብዓቶችን እንደ መነሻ በመውሰድ ተቋሙ ባለሙያዎቹን ተጠቅሞ የምርምር ሥራ መጀመሩን አስታውቀዋል፡፡
በዚህ መድረክ የቱሪዝም መሪዎች ወግ ልምዳቸውን እንዲሁም የቱሪዝም ዘርፉ እንደ ሀገር ያለበትን ተግዳሮትና ሚዲያው ላይ ባለመስራታችን እያጣነው ያለውን ገቢ ከሌሎች ሃገራት ተሞክሮ በማጣቀስ የውይይት መነሻ የሚሆን ጽሁፍ የቱሪዝም ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም አቅርቧል፡፡
ሄኖክ በመነሻ ጽሁፉ እንደገለጸው በሃገራችን የቱሪዝም ሃብት እና በዓለም ቱሪዝም ድርጅት ከተመዘገቡ ቅርሶች አንፃር በአፍሪካ አንደኛ መሆናችንን ነገር ግን በሀገር አቀፍም ሆነ በዓለም አቀፍ ሚዲያ ላይ በአግባቡ አለመጠቀማችን፣ ከቋንቋ አጠቃቀምና ስብጥር አንፃር ያለብንን ውሱንነት፣ ሁሉም በሚባል ደረጃ የሚዲያ ተቋማት ቱሪዝምን አጀንዳ አድርጎ ለመስራት ፍላጎት አለመኖር፣ በዘርፉ ላይ የሚሰሩ ጋዜጠኞች በቂ የስልጠና ለማግኘት በዘርፉ ያሉ ችግሮች መሆናቸውን ነገር ግን ኢንስቲትዩቱን ጨምሮ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ትኩረት አድርገው ቱሪዝሙ ላይ እንዲሰሩ የሚሉ ነጥቦችን አንስተዋል፡፡
የውይይቱ ተሳታፊዎችም በቀረበው ርዕስ ዙሪያ ሃሳብና አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡
ወርሃዊው የቱሪዝም መሪዎች ወግ በመጀመሪያው ዙር ኢትዮጵያዊ ቀለም ያለው መስተንግዶ እንዴት ማምጣት እንችላለን፣ ሀገር በቀል ዕውቀትና ቱሪዝም እንዲሁም ቱሪዝምና ሚዲያ በሚሉ ዕርሶች ተካሂዷል፡፡





## 4 የEASTRIP ፕሮጀክት ዕቅድ አፈጻጸም ተግዳሮቶችና መልካም ተሞክሮዎች ላይ ፕሮጀክቱ ባለባቸው ተቋማት ጋር የተደረገ ልምድ ልውውጥ

የኢንስቲትዩቱ የኢንዱስትሪ ቴክኒካል አማካሪ ቦርድ አባላት ከሀዋሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ አቻቸው ጋር የልምድ ልውውጥ አደረጉ።




የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የኢንዱስትሪ ቴክኒካል አማካሪ ቦርድ አባላት ከሀዋሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ አቻቸውና ማኔጅመንት ጋር በዓለም ባንክ በሚደገፈው የEASTRIP ፕሮጀክት ዕቅድ አፈጻጸም ተግዳሮቶችና መልካም ተሞክሮዎች ላይ የልምድ ልውውጥ አደረጉ።




ፕሮጀክቱን በአግባቡ ለመጠቀም ስራዎችን ከተቋም ዕቅድ ጋር ማስተሳሰር አስፈላጊ ነው ያሉት በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ የፕሮጀክቱ አስተባባሪ አቶ መለሰ ዲዳሞ በዓለም ባንክ አሰራር መሰረት የሚጠይቁ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ያስፈልጋል ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ተቋማቸው ከኢንዱስትሪው ጋር ከፍተኛ ትስስር በመፍጠሩ የተሻለ አፈፃፀም እንዳለ ገልፀዋል።




የማስልጠኛ ኢንስቲትዩቱ የኢንዱስትሪ ቴክኒካል አማካሪ ቦርድ አባላትና የሜኔጅመንት አባላት በፕሮጀክቱ ስራ አፈፃፀም ላይ የሚያገጥሙ ተግዳሮቶችን በመግለፅ ውይይት ተደርጓል።

የሀዋሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በሀገራችን ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር በፕሮጀክቱ እየተሰራ ከሚገኝባቸው ሶስቱ ተቋማት አንዱ ነው።

የማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር በEASTRIP ፕሮጀክት እየተከናወኑ የሚገኙ ሥራዎች ላይ ከኢንዱስትሪ ቴክኒካል አማካሪ ቦርድ ጋር ውይይት ተካሂዷል፡፡

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር በምስራቅ አፍሪካ የክህሎት ትራንስፎርሜሽንና ቀጣናዊ ትስስር ፕሮጀክት (EASTRIP) በ2015 በጀት ዓመት የተከናወኑ ሥራዎች ሂደትን ለመገምገምና የ2016 ዓ.ም ዕቅድ ላይ ከኢንዱስትሪ ቴክኒካል አማካሪ ቦርድ አባላት ጋር ውይይት አካሂዷል፡፡






የቱሪዝም ዘርፉን ለስራ እድል ፈጠራና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለመጠቀም በመንግስት ከፍተኛ ትኩረት መሰጠቱን በመክፈቻ ንግግራቸው የገለጹት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ ይህን በአግባቡ ለመጠቀም የሰለጠነና ብቃት ያለው ሰው ሀይል ወሳኝ ነው ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱ የሀገራችንን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብሮችን ተደራሽ ለማድረግ፣ ጥራትን ለማሻሻልና ስፔሻላይዜሽንን ለማጎልበት እንደሚረዳ ዋና ዳይሬክተሩ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ቴክኒካል አማካሪ ቦርዱ ኢንስቲትዩቱ ከግል ዘርፉ ጋር የተጠናከረ ትስስር በመፍጠር የኢንዱስትሪውን

በፕሮጀክቱ የተያዙ በማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ እየተከናወኑ የሚገኙ ስራዎች አፈጻጸም ለፕሮጀክቱ ዋና አስተባባሪዎች ቀርቦ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን ግብረመልስ መስጠቱን የገለጹት አቶ ገዛኸኝ አባተ ፕሮጀክቱ ኢንስቲትቱን የልህቀት ማዕከል ለማድረግ ትልቅ አቅም ስለሚሆን የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በመቅረፍ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል ብሏል፡፡




የሀገራችንን ቱሪዝም ለማሳደግ የቱሪስት መዳረሻዎችን ብቻ ማልማት በቂ ባለመሆኑ በኢንዱስትሪው ውስጥ ያለውን ብቃት ያለው የሰው ሀይል እጥረት ችግር ለመፍታት ሊሰራ ይገባል ያሉት የቴክኒካል አማካሪ ቦርዱ ሰብሳቢ አቶ መልካሙ መኮንን ፕሮጀክቱ ይህን ለመለወጥ ትልቅ መሰረት ስለሚሆን ለዕቅዱ ስኬት እንሰራለን ብለዋል፡፡




በውይይት መድረኩ ላይ የ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸምና የ2016 ዕቅድ በማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ የፕሮጀክቱ አስተባባሪ አቶ አብሃም ለገሰ የቀረበ ሲሆን በፕሮጀክቱ ማዕቀፍ የተሰሩ ሶስት የጥናት ውጤቶች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል ፡፡

**ቱሪዝም የማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ሀገር አቀፍ የቱሪዝምና ሆስፕታሊቲ አውደ ርዕይ ላይ ተሳትፏል፡፡**

በቱሪዝም ሚኒስቴር አዘጋጅነት ከአንድ መቶ በላይ የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ኢንደስትሪ ባለድርሻዎች፣ ክልሎች በተሳተፉበት አውደ ርዕይ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ተሳትፏል፡፡



በዚህ አውደ ርዕይ የማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ለሀምሳ አምስት ዓመታት በደረጃና በዲግሪ በተለያዩ የስልጠና መርሃ ግብሮች በሆቴልና ቱሪዝም የሙያ መስኮች እያሰለጠነ የቆየ፣ በዘርፉ ጥናቶችን በማካሄድና የማማከር አገልግሎቶችን በመስጠት ለሀገራችን ቱሪዝም እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ ተቋም ስለመሆኑ ራሱን አስተዋውቋል፡፡ ኢንስቲትዩቱ የተሰጡትን ሀገራዊ ኃላፊነትና ትግባራትን ለመወጣት የሚያከናውናቸውን ስራዎች በኤግዝቢሽኑ ላይ አቅርቧል፡፡

አውደ-ርዕይውን የጎበኙት የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ዝግጅቱ አገራችን ያላትን የቱሪዝም ሃብቶች የሚያስተዋውቅ መሆኑን ገልጸዋል፡፡
ጎብኚዎቹ ከህፃን እስከ አዋቂ ከተማሪ እስከ ፕሮፌሰር ፣ሴት ወንድ ሳይል፣ በውጭ ዜጎች ጭምር የተጎበኘ ነው ።
አውደ ርዕው ከመስከረም 29 እስከ ጥቅምት 28/2016 ዓ.ም የቆየ ሲሆን ስለተቋሙ መረጃዎችን በመጽሔት፣ በብሮሽር፣በካርቶን ቦርሳ፣ በቲሼርት፣ በባነር በቪዲዮና በተለያዩ መረጃ ማሰራጫዎች ለጎቢኚዎች በማሰራጨት ተቋሙ የሚሰጣቸውን ትምህርት አስመልክቶ በቂ መረጃ ተሰጥቷል፡፡





## በኢንስቲትዩቱና EASTRIP ትብብር የአሰልጣኞች ስልጠና የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን መተግበር የሚያስችል ስልጠና ተሰጠ፡፡

በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትና የምስራቅ አፍሪካ የክህሎት ትራንስፎርሜሽንና ቀጠናዊ ትስስር ፕሮጀክት (EASTRIP) በጋራ በመሆን ከአርባ አንድ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ለተገኙ የሆቴል እና የቱሪዝም አሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡



በዚህ መርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት የኢንስቲትዩቱ የትምህርትና ስልጠና ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ክብረት በዘርፉ የሚታየውን ብቃት ያለው የሰው ሀይል እጥረት ለማሻሻል ኢንስቲትዩቱ ለብቻው የሚያፈራው የሰው ሀይል ሀገራችን ካላት የቱሪዝም ዘርፉ ስፋት ጋር ሲነጻጸር አናሳ ስለሆነ በዘርፉ ስልጠና እየሰጡ ካሉ ተቋማት ጋር ተቀራርቦ መስራት ይገባል ብሏል፡፡



ስልጠናው ለዘጠኝ ቀናት የቆየ ሲሆን፣ በምግብ ዝግጅት (culinary Art)፣ ኬክና ዳቦ ዝግጅትና ቱሪዝም እንዲሁም የገቢ አስተዳደር(Revenue Management ) ላይ ያተኮረ በተግባር የተደገፈ ስልጠና ተሰጥቷል።

ሰልጣኞችም ኢንዱስትሪው ምን አይነት የሰው ሀይል እንደሚፈልግ ለመለየትና የሚሰጡትን ስልጠና ለማሻሻል እንደሚረዳቸው ገልጸዋል፡፡

ስልጠናውን ሲሰጡ ከነበሩ ከኢንዱስትሪው የተሳተፉ የምግብ ዝግጅት ባለሙያዎች መካከል ሼፍ ካብራክ ተኮላ በስልጠናው በሀገር አቀፍ ደረጃ ሙያው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የለየንበት ነው ብለዋል።

የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃላይ የጉዞ እንዱስትሪውን በቀላሉ ማስተዋወቅ በሚፈለገው ጊዜ ውስጥ መረጃ መስጠት የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን እንዴት መጠቀም እንደሚገባ የሚመለከት ከተለያዩ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ለተገኙ የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡




በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እንስትራክተር ዳዊት ኃ/ሚካኤል ሲሰጡ እንደገለጹት እየተፈጠሩ የሚገኙ ለቱሪዝም እንዱስትሪው ኢጋዥ የሆኑ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ቀላል እያደረጉ ነው ብለዋል። ቴክኖሎጂን በመጠቀም የመዳረሻ ቦታዎችን በማስተዋወቅ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ሀገራችን የዓለም ቅርስ የሆነው የቅዱስ ላልይበላ አብያተ ክርስትያናትን በቨርቹዋል ሪያሊቲ ለማስተዋወቅ የተሰራውን ሥራና በሆቴሎች ውስጥ ከአንድ ማዕከል በሲስተም የተያያዙ አገልግሎቶችን እንደምሳሌ ተጠቅሰዋል፡፡



በቱሪዝም እንዱስትሪ ውስጥ ገቢና ወጪን በመቆጣጠር የድርጅቶችን ትርፋማነት ለመጨመር የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።

የገቢ አስተዳደር (revenue management) ለድርጅቶች ያላቸውን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችና የሰው ሀይል ሀብት በዕቅድ ለመምራት የሚያስችል መሆኑን በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የሆቴል ማኔጅመንት ከፍተኛ ኢንስትራክተር እና የዘርፉ ባለሙያ አቶ ግርማይ ረዳኢ ስልጠናውን ሲሰጡ ተናግረዋል።

በኢንስቲትዩትና EASTRIP ትብብር የተሰጠ የአሰልጣኞች ስልጠና የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን ተሳታፊዎች ገልጸዋል፡፡





በሆቴልና ቱሪዝም ሙያዎች ስልጠና የሰጡት የቴክኒክና ሙያ ተቋማት መምህራን ስልጠና በኢንዱስትሪው ውስጥ የካበተ ልምድ ባላቸው የኢንስቲትዩት መምህራን እና የዘርፉ ባለሙያዎች ተግባርን መሰረት ያደረገ ስልጠና መሆኑን ተሳታፊዎች ገልጸዋል፡፡



በሐዋሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የቱሪዝም ትምህርት ኢንስትራክተር መስፍን ማቲዎስ ስልጠናው እንዱስትሪው የሚፈልገውን የሰው ሀይል እንድናሰለጥን ጥሩ ተሞክሮ እንዳገኙበት ገልጸዋል፡፡

ከፍቼ ፖሊ ቴክኒክ የመጡት በስልጠናው ላይ ብዙ የማሰልጠን ልምድ ካላቸው መምህራን ጋር መሰልጠንና  በተለይም በሙያው ጥሩ ልምድ ባላቸው መምህራን መሰጠቱ እንደ ሀገር ያለውን የአሰልጣኞችን ግንዛቤ ወደ ተመሳሳይ ደረጃ ለማምጣት ይረዳል ብሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ከላሊበላ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ እና ከአርባምንጭ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ስልጠናውን እየተካፈሉ የሚገኙት ብቃት ያለውን ሰልጣኝ ለማፍራት እንደሚረዳቸው ገልጸዋል፡፡ ስልጠናው በመስከረም ወር የተሰጠ ነው፡፡

**የማማከር አገልግሎት በቱሪስት መዳረሻዎችና ሆቴሎች ላይ ተሰጠ ።**



ቱሪዝም ማስልጠኛ ኢንስቲትዩት የምርምርና ማማከር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ስዩም ተቋሙ ከተሰጠው ተልዕኮ አንዱ የማማከር እና የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት በመስጠት ማህበረሰቡን መደገፍ መሆኑን ጠቁመው ፤ ዘንድሮ ከተያዙ ዕቅዶች ለመጀመሪያ ዙር በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ 71 ድርጅቶች የማማከር አገልግሎት በስምንት ከተሞች መሰጠቱን  ገልጸዋል፡፡

የማማከር አገልግሎቱ ዓላማ የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች ወደ የከተሞቹ ሆቴሎችና የቱሪስት መዳረሻዎች መንቀሳቀሳቸው ስለማይቀር ሙያዊና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ፣ የውስጥ አደረጃጀታቸውን እንዲያሻሽሉ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ነው፡፡



በአገልግሎቱ ሆቴሎች ባለ ኮኮብእና ወደ ኮኮብ ሆቴልነት እያደጉ ያሉት ተካተዋል። የዶሽ ሆቴል ሥራ አስኪያጅ አቶ አለሙ እንደተናገሩት ይህ አይነት የማማከር አገልግሎት ሰፊ ጊዜ ተወስዶ የሚሰጥ ቢሆን የተሻለ እንደሆነና አጭር ሰዓት ቢሆንም ጥሩ ልምድ እንዳገኙ ተናግረዋል።



በሌላ ዜና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚገኙ ለተመረጡ ሆቴሎች የማማከር አገልግሎት ተሰጠ።

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከአዲስ አበባ ባህል ቱሪዝም ኪነ ጥበብ ቢሮ ጋር በመተባበር በከተማው የሚገኙ እና የተመረጡ 84 ሆቴሎችን አቅም የሚገነባ የማማከር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

አገልግሎቱ በዋናነት በእንግዳ አቀባበል እና መስተንግዶ ፣ በምግብ አዘገጃጀት ፣ በቤት አያያዝና ንፅህና አጠባበቅ ዙሪያ የማማከር ሥራ እየተሰራ መሆኑን የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ስዩም ገልጸዋል።

እንደ ም/ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ አገልግሎቱ ከአዲስ አበባ ከተማ በተወጣጡ 20 የሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች የኢትዮጵያ ሆቴል ምደባ መስፈርትን መሰረት በማድረግ ስልጠና በመስጠት ወደ የተቋማቱ ሄደው የማማከር አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል።

አገልግሎቱ መጭዉን የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ምክንያት በማድረግ ጭምር የተሰጠ ሲሆን፤ ሆቴሎች የኮከብ ደረጃ እንዲያገኙ እና ያላቸውንም እንዲያሻሽሉ የሚያግዝ ነው።

የማማከር አገልግሎት ካገኙ ተቋማት መካከል የታሪካዊዉ ጣይቱ ሆቴል እና የጃቫኒ ሆቴል ሥራ አስኪያጆች እንደገለፁት ተቋሙ ተነሳሽነት በመውሰድ እንደዚህ አይነት የማማከር አገልግሎት መሰጠቱ የሚበረታታ መሆኑን በመግለፅ ከዚህ በኋላ በአጫጭር ስልጠና እና በማማከር አገልግሎት ዙሪያ ከተቋሙ ጋር አብረው እንደሚሰሩ ተናግረዋል።

# የስድስት ወር ዕቅድ አፈጻጸም ቀረበ



ቱ.ማ.ኢ. ጥር 18/2016 ዓ
የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የ2016 ዓ.ም የግማሽ ዓመት ሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለሰራተኞች ቀረበ።
የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ እንደገለጹት ባለፉት ስድስት ወራት ከዝግጅት ምዕራፍ ጀምሮ የተሰሩ ሥራዎችን ከስር ከስሩ እየገመገምን የመጣን ቢሆንም አሁን ላይ ቀሪውን የስድስት ወር አፈፃፀም የተሻለ ለማድረግ ያለፈውን መገምገም ብቻ ሳይሆን የመረጃ ልውውጥ በማድረግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።





የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቱን የዕቅድ ክፍል ተ/ ዳይሬክተር አቶ ተመስገን በቀለ እና የለውጥና መልካም አስተዳደር ሥራዎች ክንውን በአቶ ሰለሞን አሰፋ የለውጥና መልካም አስተዳደር ተ/ ዳይሬክተር ቀርቧል።
በሪፖርቱ ከዚህ በፊት በሰራተኛው ቅሬታ ቀርቦባቸው መልስ ያገኙ፣ እየተሰሩ ያሉ እና ያልተፈቱ ያሏቸውን እና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች አንስተዋል። በቀረበው ሪፖርት ከሰራተኛው አስተያየትና ጥያቄ ቀርቧል።









በከሰዓት ፕሮግራም የሥራ ላይ ጤንነት እና ጤናማ የሥራ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስችል አካላዊ ፣ስነልቦናዊ እና ኢኮኖሚያዊ ስልጠና በዶ/ር ሰላም አክሊሉ የዌልነስና ካሮፕራክቲክ ክሊኒክ ባለቤት ተሰጥቷል። ዶ/ር ሰላም አክሊሉ አስር ለጤና፣ ከቤት እስከ መስሪያ ቤት በሚል ስልጠና በስጠት ይታወቃሉ ።

## EASTRIP ፕሮጀክት ተቋሙን የሥልጠናና የምርምር ሥራዎች እየደገፈ መሆኑ ተገለጸ።





ቴ.ማ.ኢ

ጥር 19/2016 ዓ ም

EASTRIP ፕሮጀክት ተቋሙን የሥልጠናና የምርምር ሥራዎች እየደገፈ መሆኑን የፕሮጀክቱ አስተባባሪ አቶ አብርሃም ለገሰ የአራት ወር የሥራ አፈፃፀም ለሠራተኛው ባቀረቡበት ወቅት ተናግረዋል።

የፕሮጀክቱ የፋይናንስ አፈፃፀም በጥሩ እየተመራ በመሆኑ ቀጣይ ሥራዎችም በትኩረትና በጥብቅ ክትትል እንዲፈጸሙ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ የሥራ መመሪያ ሰጥተዋል።

የቀጣይ የስድስት ወር ሥራዎችን ዕቅድ መከለስ የሚያስፈልጋቸውን በመከለስ ሥራዎች በተያዘላቸው ጊዜ እንዲከናወኑ በማሳሰብ የፕሮግራም ማጠቃለያ ተደርጓል።





## በሆቴልና በቱሪዝም ዘርፍ የዲግሪ ካሪኩለም ማሻሻያ እና የክህሎት ውድድር ማስፈጸሚያ ሰነድ ተዘጋጀ።

ቱ ማ ኢ

ህዳር 23/2016 ዓ ም

በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በሆቴልና በቱሪዝም ዘርፍ የዲግሪ ካሪኩለም ማሻሻያ እና የክህሎት ውድድር ማስፈጸሚያ ሰነድ ተዘጋጀ። የተቋሙ የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ክብረት እንደገለጹት ከዚህ በፊት የክህሎት ውድድር የሚካሄድ ቢሆንም ደረጃውን የጠበቀ ሰነድ ባለመኖሩ ወጥ ውድድር እንዳልነበረ በመጠቆም ውድድሮቹ በቋንቋም እንዲደገፉ በማድረግ ቀጣይ የሚኖሩ የክህሎት ውድድሮችን በተሳካ ሁኔታ ለማስፈጸም የሚረዳ ሰነድ ማዘጋጀት እንዳስፈለገ ተናግረዋል።



በመቀጠልም የካሪኩለም ዝግጅቱን በተመለከተ የተቋሙ ምርምርና ማማከር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ስዩም እንደተናገሩት ካሪኩለም ማሻሻያ ያስፈለገው ከዚህ በፊት ከሌሎች ኮፒ ተደርጎ ይሰራበት እንደነበረና አሁን ተቋሙ ተግባር ተኮር በመሆኑ የትምህርትና ስልጠና ፖሊስ ምክንያት እንዲሁም በቅርቡ ተቋሙ ያጠናቸው ጥናቶች ለዚህ ካሪኩለም ማሻሻያ መነሻ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በሰነድ ዝግጅቱ አምስት ኮርሶች ለኢንዱስትሪው እንደሚቀርቡ ተጠቅሟል። በሁለቱም ሰነድ ዝግጅቶች ላይ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ካሪኩለም ዝግጅት ከፍተኛ ባለሙያዎች እና የኢንዱስትሪው ባለቤቶች ተሳትፈውበታል።

ሁል ጊዜ በተቋሙ የሚሰጠውን የስልጠና ጥራት ለማሻሻል እንዲሁም የተቋሙን ገጽታ ለመገንባት የሚያግዘው EASTRIP ፕሮጀክት ጋር በመተባበር እንደሆነ ተገልጿል።



**"የሠራተኛውን የኑሮ ጫና የሚያቃልሉ አማራጮችን ሁሉ በመጠቀም ዘላቂ ተጠቃሚ እንዲሆን እንሰራለን። "አቶ ገዛኸኝ አባተ የኢንስቲትዩቱ ም/ዋና ዳይሬክተር ቱ.ማ.ኢ**







ህዳር 28/2016 ዓ.ም
የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሰራተኞች የህብረት ስራ ማህበር በማቋቋም በዘላቂነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ስለ ጉዳዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።
ስልጠናውን ያስጀመሩት የኢንስቲትዩቱ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ሰራተኞች በህብረት ሥራ ማህበር በመደራጀት ያለውን የኑሮ ጫና ለመቋቋምና በዘላቂነት ተጠቃሚ ለመሆን እንደሚያግዝ ገልጸው የሠራተኛውን የኑሮ ጫና የሚያቃልሉ አማራጮችን ሁሉ በመጠቀም ዘላቂ ተጠቃሚ እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ይደረጋል ብለዋል።
የህብረት ሥራ ማህበር የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች የሚያቋቁሙት የንግድ ማህበር መሆኑን የገለጹት በህብረት ሥራ ኮሚሽን የህብረት ሥራ ማህበር መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ድሪባ በቀለ በገበያ ውስጥ የመደራደር አቅምን የሚጨምርና በፍትሐዊነት ከግብይት ተጠቃሚ ለመሆን ያስችላል ብለዋል።
ከሰራተኞች ለቀረቡ ጥያቄዎች ከህብረት ሥራ ኮሚሽኑ ባለሙያ ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቷል።

## ከወረዳ 11 ለተወጣጡ ሴቶችና ወጣቶች በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጣ

ቱ. ማ. ኢ









ታህሳስ 10/2016 ዓ.ም
የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ለማስፋት በቂርቆስ ክ/ከተማ ከወረዳ 11 ለተወጣጡ ሴቶችና ወጣቶች በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ስልጠና ተሰጠ።
ስልጠናውን አስመልክቶ በተቋሙ የጥናትና ምርምር ክፍል ባለሙያ አቶ ሄኖክ መሐሪ እንደተናገሩት ከወረዳ 11 ሴቶችና ህጻናት ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ምንነትና ዘርፉ የሚያስገኘውን የሥራ እድል አስመልክቶ በተለያዩ አሰልጣኞች ሰልጠና ለመስጠት መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል፡፡
ስልጠናውን የሰጡት አሰልጣኞች አቶ ሰይድ ተስፋዬ በምግብና መጠጥ መስተንግዶ ፣ አቶ ሀብቱ ተካ በቤት አያያዝና እንግዳ አቀባበል አቶ በቀለ ኡማ በቱሪዝም ዘርፍ የሚገኙ የሥራ ዕድሎችን የአንድ ቀን ግንዛቤ ማስጨበጫ ሰጥተዋል፡፡
ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ከተሰጡት ተልእኮዎች አንዱ የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት መስጠት ሲሆን እስካሁን በተለያዩ አገልግሎቶች የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ እያደረገ መሆኑ ይታወቃል ።

## ለቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት አሰልጣኞች የማስተማር ስነ ዘዴ ስልጠና ተሰጠ ።



ቱ ማ ኢ
ህዳር 1/2016 ዓ ም
ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የሰልጣኞችንና የስልጠና እርካታ ለማሻሻል እንዲሁም የኢንዱስትሪውን ፍላጎት በዕውቀት በክህሎትና በስነምግባር የተደራጀ ባለሙያ ለማቅረብ የሚያስችል የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ስልጠና ተሰጣቸው ።

በመክፈቻው የተገኙት የተቋሙ የስልጠናና አቅም ግንባታ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ክብረት እንደገለጹት ይህ ስልጠና አዲሱን የትምህርት ፖሊስ ወደተግባር ለመቀየር የሚረዳ መሆኑን በመጠቆም 12ኛ ክፍል የጨረሰ ተማሪ የእጅ ሙያ ይዞ የሚመረቅ እንደሆነ አዲሱ ትምህርት ፖሊስ ይገልጻል። እነዚህ ተማሪዎችን በፍላጎታቸው ወደ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ሲመጡ ተማሪ ተኮር በሆነ ስነ ዘዴ ለማስተማር ይህ ስልጠና አስፈላጊነት የጎላ ነው ብለዋል።



ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የልህቀት ማዕከል ሆኖ ለመገኘት የመምህራን አቅም ግንባታ ወሳኝ በመሆኑ ከእስትሪፕ (EASTRIP)ፕሮጀክት ጋር በመተባበር የተለያዩ ስልጠናዎች ልምድ ልውውጦች በቀጣይ እንደሚኖሩ አቶ ሀብታሙ ክብረት ተናግረዋል።

ይህን ሰልጠና በጥሩ ስነምግባር መከታታል እንዳለባቸው አሳስበዋል።

የስልጠናው ዓላማ የተቋሙን ገጽታ ለመገንባት ፣ የኢንዱስትሪውን ፍላጎት በዕውቀት በክህሎትና በስነምግባር የተደራጀ ባለሙያ ለማቅረብ ሲሆን ይህም ስልጠና በተለያዩ ምርምር ውጤቶችና ስብሰባዎች ከተገኙ መነሻ ሀሳብ ተወስዶ እንደሆነ የኢስትሪፕ(EASTRIP) ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ አብርሃም ለገሰ ተናግረዋል።




ይህ ፕሮጀክት ተቋሙን ወደ ልህቀት በሚያደርሱ ሥራዎችና የአሰልጣኞችን አቅም ግንባታ በጥናት ላይ በመመሥረት የሚሰራ በመሆኑ የታዩትን ክፍተቶች ለመሙላት ከሌሎች ተቋማት የጋር ስራዎችን ይሰራል ።

ስልጠናውን የሰጡት ከፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩቱ የካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ረዳት ፕሮፌሰር ዶ/ር አለማየሁ ሀብቴ እና የካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ሌክቸር አቶ ንጉሤ አሎሎ ናቸው።






ሌላው የኮርስ ካታሎግ ማሻሻያ፣ የሪጂስትራር አሰራሮችን በተመለከተና የኳሊቲ አሹራንስ ሥራዎች ማሻሻያ እየተደረገ ነው። ማሻሻያ የሚደረግባቸው ከዚህ በፊት የሚነሱ ውስንነቶችን ማስተካከል ባለባቸው ጉዳዮች በመወያየት ውሳኔ ሀሳብ ላይ እንደሚደረስ የአጠቃላይና ደጋፊ ትምህርት አስተባባሪ አቶ ዋቅጅራ ረቡማ ተናግሯል።



እነዚህ ስራዎች ሁሉ ተቋሙ ወደ ልህቀት ማዕከልነት የሚያደርገውን ጉዞ የሚያስፈፅሙ ተግባራት ናቸው። ይህም አቅም ግንባታ ስራ በዚህ የሚያበቃ አለመሆኑ በአስተባባሪው ተገልጿል።

# ለኢንዱስትሪ አሰልጣኞች የማሰልጠን ስነ ዘዴ ስልጠና ተሰጠ




ቱ. ማ ኢ

ታህሳስ 24/2016 ዓ ም

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የራሱን አሰልጣኞች ወደ ኢንዱስትሪው ለትብብር ስልጠና በሚልክበት ጊዜ ያለውን መስተጋብር ለማዘመን የሚረዳ የኢንዱስትሪ አሰልጣኞች የማሰልጠን ስነ ዘዴ ተሰጠ።

ስልጠናውን በንግግር የከፈቱት የተቋሙ የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ክብረት እንደገለጹት ሰልጣኞችን ለትብብር ስልጠና ወደ ኢንዱስትሪ በሚልክበት ጊዜ ያለውን መስተጋብር ለማዘመን የሚረዳ ነው ብለዋል።

ይህ ስልጠና ብቃት ያለው የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራትና ለሰልጣኞች የሙያ ደረጃዎች ለማሻሻልም እንደሚጠቅም ገልጸዋል።

ስልጠናው በተቋማችን አሰልጣኝ በአቶ ዳንኤል በቀለ ስለትብብር ስልጠና ምንነትና የኢንዱስትሪው የተቋሙ እና የሰልጣኙ ተግባርና ኃላፊነትን በተመለከተ ተሰጥቷል፡፡

የሁለተኛው ቀን ስልጠና የሰጡት የተቋማችን አሰልጣኝ ወ/ሪት እታፈራሁ ሲሳይ የመምህሩ የማስተማሪያ ሰነድ አዘገጃጀትና በውስጡ መካተት ያለባቸው ተግባራት እንዲሁም ሰልጣኙን እንዴት መገምገም እንደሚቻል በተግባር የተደገፈ ስልጠና ሰጥተዋል።

በማጠቃለያው ፕሮግራም ላይ የተገኙት የኢንስቲትዩት ትብብር ስልጠና አስተባባሪ ና አሰልጣኝ ታደሰ ሞላ እንደገለፁት ይህ ስልጠና በዚሁ የሚቀር ሳይሆን በቀጣይነት ወደ ተግባር የሚቀየር እንደሆነ በመጠቆም አሰልጣኞቻችን ወደ ኢንዱስትሪ በሚሄዱበት ወቅት የሚገጥማቸውን ክፍተቶች ለመሙላት አሁን ከሰለጠኑ ባለሙያዎች የሚጠበቅ መሆኑን ገልጸዋል።

ለሰልጣኞቹ በስልጠናው ዙሪያ መመዘኛ በመስጠት ሰርተፍኬት ተሰጥቷቸዋል።

ሰልጣኞችም በስልጠናው በጣም እንደተደሰቱና ከተቋሙ ጋር በትብብር ስልጠናም ይሁን በሌላ አብሮ እንደሚሰሩ ገልጸዋል









